# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ዶሮና ንስር

Written by: Ann Nduku
Illustrated by: Wiehan de Jager
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 3.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/3.0

# ዶሮና ንስር



Ann Nduku
Wiehan de Jager
Dawit Girma
Amharic
Level 3



በድሮ ጊዜ ዶሮና ንስር ጓደኛሞች ነበሩ። ከሌሎች የወፎች ዘር ጋርም በሰላም ይኖሩ ነበር። አንዳቸውም መብረር አይችሉም ነበር።





የንስር ክንፍ ጥላ መሬቱ ላይ ባረፈ ጊዜ ዶሮ ጫጩቶቿን ታስጠነቅቃለች። <<ግልጽ ቦታ ላይ አትሁኑ፣ ጥፉ አምልጡ!>> ጫጩቶቹም እንዲህ ይላሉ፦ <<ሞኞች አይደለንም፣ እንሮጣለን።>>



ንስር በቀጣይ ቀን ስትመጣ ዶሮ አሸዋውን እየጫረች አገኘቻት፤ ግን መርፌ የሚባል የለም። ከዚያ ንስር ዝቅ ብላ በፍጥነት በመብረር ከዶሮዋ ጫጩቶች አንዷን ቀለበቻት። ይዛትም ርቃ በረረች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ንስር ብቅ ባለች ቁጥር ዶሮ መርፌውን ፍለጋ አሸዋውን ስትጭር ታገኛታለች።





አንድ ወቅት፣ በምድር ሁሉ ላይ ረሃብ ተከሰተ። ንስር በጣም ራቅ ያለ ቦታ ሄዳ ምግብ መፈለግ ነበረባት። ከዚያም በጣም ደክሟት ተመለሰች። ‹‹ለመጓዝ በጣም ቀላል ዘዴ መኖር ነበረበት›› አለች ንስር።



ሌሊቱን ጣፋጭ እንቅልፍ ካሳለፈች በኋላ ዶሮ ግሩም ሃሳብ መጣላት። ከሌሎች ወፎች የወዳደቀ ላባ ሁሉ መልቀም ያዘች። ‹‹በሉ ከእኛ ላባ ላይ እነዚህን አብረን እናያይዛቸው›› አለች። ‹‹ምናልባት ይሄ ለመጓዝ ቀላል ያደርግልን ይሆናል››





‹‹አንድ ቀን ብቻ ስጪኝ›› ብላ ዶሮ ንስርን ተለማመጠቻት። ‹‹ከዚያ ክንፍሽን ጠግነሽ ዳግም ምግብ ፍለጋ መብረር ትችያለሽ።›› ‹‹አንድ ተጨማሪ ቀን ብቻ›› አለች ንስር። ‹‹መርፌውን ማግኘት ባትችዪ ግን ከጫጩቶችሽ አንዷን እንደክፍያ ትሰጭኛለሽ።›› አለቻት።



ወደማታ ግድም ንስር ተመለሰች። በጉዞ ወቅት የላሉ
አንዳንድ ላባዎችን ለመጠገን ፈልጋ መርፌውን ጠየቀች።
ዶሮ መሳቢያው ስውጥ ተመለከተች፣ ማዕድ ቤት
ፈለገች፣ በግቢው ውስጥም አየች። ነገር ግን መርፌው
የትም መገኘት አልተቻለም።





ንስር በሰፈሩ መርፌ ያላት ብቸኛዋ ነበረች። ስለዚህ
መጀመሪያ መስፋት ጀመረች። ለራሷ የሚያምር ጥንድ
ክንፍ ሰራችና ከዶሮ በላይ መብረር ጀመረች። ዶሮ መርፌ
ተዋሰች። ስትሰፋ ግን ወዲያውኑ ደከማት። መርፌውን
መሳቢያ ውስጥ አስቀምጣ ለልጆቿ ምግብ ለማብሰል
ወደ ማድቤት ገባች።



ሌሎቹ ወፎች ንስርን ርቃ ስትበር ተመልክተዋታል። ከዚያም ዶሮን ለራሳቸውም ክንፍ ለመስራት እንዲችሉ መርፌውን ታውሳቸው ዘንድ ጠየቋት። ወዲያው ወፎች በሰማዩ ላይ ከፍ ብለው ይበሩ ጀመር።





የመጨረሻዋ ወፍ የተዋሰችውን መርፌ ስትመልስ ዶሮ በቦታው አልነበረችም። በመሆኑም ልጆቿ መርፌውን ይዘው ይጫወቱበት ጀመር። ተጫውተው ሲደክማቸው፣ መርፌውን አሸዋ ውስጥ ተውት።